# ከጽዮን እስከ አክሱም ጽዮን

ከጌታቸው በቀለ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከምታከብራቸው የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በዓላት አንዱ «ኅዳር ጽዮን» ሲሆን የሚከበረውም ኅዳር 21 ቀን ነው፡፡ የበዓሉን አከባበር ጥንተ ታሪኩንና ሌሎችም ተያያዥ ጉዳዮችን እንመለከታለን፡፡

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን «ታቦተ ጽዮን» የፈጸመችውን ልዩ ልዩ ተአምራት ለምእመናን እያስተማረች በታላቅ ድምቀት የምታከብረው ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ሊቀ ነቢያት ሙሴ በደብረ ሲና አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከጾመና ከጸለየ በኋላ ዐሠርቱ ቃላት የተጻፈበትን ጽላት /ታቦተ ጽዮን/ ከእግዚአብሔር እጅ ተቀበለ፡፡«ታቦተ ጽዮን» የሚለውንም ስያሜ ያገኘችው ጽዮን ተብላ በምትጠራው የእስራኤል ከተማ ስም ነው፡፡ ጽዮን ማለት ተፀወነ፡- ተጠጋ፣ ተማጠነ ማለት ነው፡፡ ክቡር ዳዊትም ጽዮንን አንባ፣ መጠጊያ አድርጐ ብዙ ጠላቶቹን ተዋግቶ አሸንፎ ድልን ተጐናጽፏል፡፡

ጽዮን የተባለችው የታላቁ የዳዊት ከተማ የተገፉና የተበደሉ ሕዝቦች ሁሉ እውነተኛ ፍርድ ለማግኘት፣ ተሰብስበው የሚሰነብቱባት ከተማ ስለነበረች፤ ጽላተ ሙሴም በዚያ ስለነበረች በርሷ ተማጽነውም ችግራቸው ስለሚቃለል ታቦቷ «ታቦተ ጽዮን» ተብላለች፡፡

ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ በራእዩ «በሰማይ ያለችው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ተከፈተች፡፡ በውስጧም ያለችው ታቦተ ሕግ ታየች፡፡» ራእይ.11ሚ19 በማለት የተናገረውን ቅዱስ ኤጲፋንዮስ በመጽሐፈ አክሲማሮስ ሲተረጉመው «በሥላሴ ጸዲል በሥላሴ ብርሃን የተመላች ስመ ሥላሴ የተጻፈባት ታቦት በኢየሩሳሌም ሰማያዊት አለች፡፡ በዚህች ታቦት ላይ ከፍጥረት ዓለም በፊት ስመ እግዝእትነ ማርያም ተጽፎባት ነበር፡፡ ቅድመ ዓለም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከመፈጠሯ በፊት በአምላክ ኅሊና ታስባ ትኖር ነበር የሚለው መሠረቱ ይህ ነው» ብሏል፡፡ ታቦተ ጽዮን የምትኖርበትን ድንኳን ሊቀ ነቢያት ሙሴ እንዲሠራ እግዚአብሔር ነግሮታል፡፡ ሊቁ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ሲናገር «ደብተራ ኦሪትን በኢየሩሳሌም ሰማያዊት አርአያና ምሳሌ እንዲሠራ እግዚአብሔር አሳይቶታል፡፡ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ሁለንተናዋ ከብርሃን የተሠራች ናት፡፡ የኢየሩሳሌም ሰያዊት ቀርጹም ደብተራ ኦሪትን ትመስላለች፡፡» ይላል፡፡ ሕዝቡም ከፈጣሪያቸው ጋር ቃል ኪዳን ገብተው በታቦተ ጽዮን አማካኝነት ሲያመሰግኑ ኑረዋል፡፡

ታቦተ ጽዮን እግዚአብሔርን ለሚያምኑ፣ ሕጉን ትእዛዙን ለሚፈጽሙ ሰዎች ሁሉ ልዩ ልዩ ተአምራትን እንደፈጸመች ከቅዱስ መጽሐፍ እንረዳለን፡፡ እስራኤላውያን ሕጉን ሲጠብቁ ትእዛዙን ሲፈጽሙ እግዚአብሔር በታቦተ ጽዮን እያደረ ይረዳቸውና ጠላቶቻቸውንም ድል ያደርጉ ነበር፡፡ ሕጉን ሲያፈርሱ ደግሞ በጠላቶቻቸው ይሸነፉ ነበር፡፡

በዚያ ዘመን ኤሊ የሚባል ሊቀ ካህናት ነበር፡፡ አፍኒንና ፊንሐስ የሚባሉ ሁለት ልጆች ነበሩት፡፡ እድሜውም 98 ዓመት ነበር፡፡ አፍኒንና ፊንሐስ የአባታቸውን ምክር አቃለው የማይገባ ኃጢአት ሠርተው አምላካቸው እግዚአብሔርን አሳዘኑ በራሳቸው ፈቃድ ተጉዘው ሕገ እግዚአብሔርን ጣሱ፡፡ በሕዝቡም ላይ የሚያደርሱት በደል እየጨመረ ሔደ፡፡

አፍኒንና ፊንሐስ እግዚአብሔር በኃጢአታቸው ምክንያት በረድኤት ስለተለያቸው ፍልስጥኤማውያን በጠላትነት ተነሡባቸው፡፡ እስራኤላውያን ከኤሊ ልጆች ጋር ሆነው በአንድነት ታቦተ ጽዮንን ይዘው ለጦርነት ወደ ፍልስጥኤም ዘመቱ፡፡ ጦርነትም ገጠሙ ታላቅ ግድያም ሆነ፡፡ በጦርነቱ አፍኒንና ፊንሐስ ሞቱ፡፡ ታቦተ ጽዮንም በኤሎፍላውያን እጅ ተማረከች፡፡ ሕዝቡም በጦርነት አለቁ፡፡ ከጦርነቱ ያመለጠ አንድ ሰው ወደ ኤሊ ሄዶ እስራኤላውያን ተሸንፈው መሸሻቸውን፤ ሁለቱ ልጆቹ አፍኒንና ፊንሐስ መሞታቸውን ታቦተ ጽዮንም መማረኳን ነገረው፡፡ ኤሎፍላውያንም ታቦተ ጽዮንን ማርከው ከወሰዷት በኋላ ዳጐን ከተባለው ጣዖታቸው በታች አስቀመጧት፡፡ በማግስቱ የዳጎን አገልጋዮች መጥተው ቢያዩአት፤ ዳጎን ከእግዚአብሔር ታቦት ፊት በግንባሩ ተደፍቶ አገኙት፡፡ አንስተው አቁመውት ሔዱና በማግስቱ መጥተው ቢመቱት በግንባሩ ወድቆ እጆቹ ተለያይተው ጣቶቹም ተቆራርጠው ደቀው በወለሉ ላይ ተበታትነው ነበር፡፡ ታቦተ ጽዮን ግን ምንም ጉዳት ሳይደርስባት ከላይ ሆና አገኙአት፡፡ አገልጋዮቹም ታቦተ ጽዮን ያደረገችውን ተአምር በማድነቅ ዳጎንን በመናቅና በማቃለል ከዚያ ቀን ጀምረው ከቦታው ፈጽመው አልደረሱም፡፡ 1ኛ ሳሙ.5÷1-7፡፡ ሕዝቡም በሰውነታቸው ላይ እባጭ እየወጣባቸው ሲገድላቸው ሌሎቹንም በሚያንቀጠቅጥና በሚጥል በሽታ እያሰቃያቸው፣ እህላቸው በዓይጥ፣ እንስሶቻቸው በበሽታ አለቁባቸው፡፡

ታቦተ ጽዮን በኤሎፍላውያን ላይ እንዲህ ያለ ተአምር እየፈጸመች በፍልስጥኤም አገር ለሰባት ወራት ቆይታለች፡፡ ከሰባት ወራት በኋላ ኤሎፍላውያን ታቦተ ጽዮንን ወደ ሀገሯ ለመመለስ ወርቅ በሳጥን

አድርገው በሠረገላ ጭነው በላሞች እያስጐተቱ ወደ ሀገሯ ሰደዷት፡፡ እስራኤላውያን የተቦተ ጽዮንን መመለስ በሰሙ ጊዜ በዕልልታ በሆታና በዝማሬ ተቀብለው አሚናዳብ ቤት አስገቧት፡፡ በዛም ሃያ ዓመታት ኑራለች፡፡ የአሚናዳብ ቤት በታቦተ ጽዮን ምክንያት ተባርኮለታል፡፡ 1ኛሳሙ.7÷2፡፡

ንጉሥ ዳዊት ታቦተ ጽዮን ወደ ከተማው በመጣች ጊዜ ከዙፋኑ ተነስቶ እየዘመረ በክብርና በምስጋና ተቀብሏታል፡፡ ብዙ መስዋዕትም ተሰውቷል፡፡ 2ኛ ሳሙ.6÷14፡፡ ታቦተ ጽዮን እስከ ንጉሥ ሰሎሞን ዘመን ድረስ በድንኳን /በደብተራ ኦሪት/ ከተቀመጠች በኋላ በንጉሡ ሰሎሞን በተሠራው ቤተ መቅደስ ገብታለች፡፡ 1ኛ ነገ.8÷1-12፡፡

## የንግሥተ ሳባ ጉዞ ወደ ኢየሩሳሌም

ከጌታችን ልደት በፊት በ1ሺ ዓ.ዓ በኢትዮጵያ የነገሠችው ንግሥት ሳባ ሦስት ስም አላት፡፡ በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ምዕራፍ10÷1-10 እና በ2ኛ ዜና.9÷1-8 ላይ «ሳባ» በማለት ትጠራለች፡፡ በክብረ ነገሥት ደግሞ «**ማክዳ**» ተብላለች፡፡ ጌታችን በመዋዕለ ትምህርቱ «**ንግሥት አዜብ**» ብሏታል፡፡ ማቴ.12÷42፡፡ አዜብ ማለት ደቡብ ማለት ሲሆን ኢትዮጵያ በድሮ ግዛትዋ ለእስራኤል ደቡብ ነበረች፡፡ ጌታ ንግሥት አዜብ ያላትም ለዚህ ነበር፡፡ ይህንን ቃል ከእርሷ በኋላ 1500 ዓመት ቆይተው የተነሱት የኢትዮጵያ ነገሥታት ሳይቀሩ ይጠቀሙበት እንደነበር የቤተ ክርስቲያን መዛግብት ያስረዳሉ፡፡

ስለ ንግሥት ሳባ ኢትዮጵያዊነት የሚያስረዱ የተለያዩ ማስረጃዎች ይገኛሉ፡፡ ከጥንታውያን የታሪክ ጸሐፍት መካከል የሚቆጠረው ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን ስለዚህችው ንግሥት «በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያና የግብጽ ንግሥት የነበረችው» በማለት ነበር የጻፈው፡፡ ላዕላይ ግብጽ ከጥንት ጀምሮ የኢትዮጵያ ግዛት እንደነበር የታወቀ ነው፡፡ የግብጻውያን ትልቁ የታሪክ መዝገብ የሆነው የትርያርኮች ታሪክም እንዲህ ይላል «የታላቁ ሀገር አቢሲኒያ ንግሥት እርስዋም ንግሥት ሳባ የምትባል የደቡብ ንግሥት፤ ወደ ዳዊት ልጅ ሰሎሞን መጣች፡፡» ይላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በኢትዮጵያችን ከንግሥት ሳባ ጋር የተያያዙ ልዩ ልዩ የአርኪዎሎጂ /የከርሰ ምድር ጥናት/ ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡

የንግሥተ ሳባ ትውልድ ቦታ ፡- በሰሜን ደንገሎ፣ በደቡብ ፎካደ በተባሉ በሁለት ተራሮች መካከል የሚገኝ ሲሆን ስሙም «ጐሎ ማክዳ» ይባላል፡፡

የንግሥተ ሳባ መቃብር፡- ከአክሱም ወደ ጎንደር በሚወስደው መንገድ ዳር በስተደቡብ 2ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡

የንጉሥ ምኒልክ አንደኛ መቃብር፡- አክሱም ከተማ በስተምዕራብ 2ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ በ1906 የደች ልዑካን የአርኪዎሎጂ ጥናት በሚያደርጉበት ወቅት ከምድር ውስጥ በተቀበረ ቤት ውስጥ የንጉሥ ምኒልክን ዐጽም ያገኙ ሲሆን የአክሱም ጽዮን ካህናት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በክብር እንዳሳረፉት ይታወቃል፡፡

በ13ኛው መ/ክ/ዘመን የነበሩት የአክሱም ንቡረ ዕድ ይስሐቅ ከተለያዩ ምንጮች ክብረነገሥትን ሲያዘጋጁ እጅግ ታላቅ ቦታ ከሰጡዋቸው ታሪኮች መሐል አንዱ የንግሥት ሳባ ታሪክ ነው፡፡ ንግሥት ሳባ እግዚአብሔርን በመፍራት በመልካም ሁኔታ ሕዝቡን ታስተዳድር ነበር፡፡ በወቅቱ በእስራኤል ላይ ነግሦ የነበረውን የሰሎሞንን ጥበብ በጆሮ መስማት ብቻ በቂ ሆኖ ስላላገኘችው በዓይን አይቶ መረዳት የበለጠ መሆኑን ተገነዘበች፡፡

ለንግሥት ሳባ ወደ ኢየሩሳሌም መጓዝ ምክንያት የሆናት ታምሪን የተባለው ነጋዴ ነው፡፡ ይህ ነጋዴ በኢየሩሳሌም በሚቆይበት ጊዜያት ብዙውን ጊዜ የማያሳልፈው የሰሎሞንን ሥጋዊና መንፈሳዊ ጥበብ በማየት ነው፡፡ ወደ ኢትዮጵያ በሚመለስበትም ጊዜ እየዘረዘረ ለንግሥት ሳባ ይነግራትና ያስረዳት ስለነበር፤ ንግሥት ሳባ ከዚሁ ነጋዴ በሰማችው ዜና የንጉሥ ሰሎሞንን ጥበብ ለማየት ጓጓች፡፡ በዚህም የተነሣ በታምሪን መሪነት ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዘች፡፡ እግዚአብሔርም መንገዱን አቀናላት፤ ያለአንዳች መሰናክል ተጉዛ ኢየሩሳሌም ደረሰች፡፡ ለታቦተ ጽዮን ክብርና ለንጉሥ ሰሎሞንም ገጸ በረከት አቀረበች፡፡ 1ኛ ነገ.10ሚ1-13፡፡

ንጉሥ ሰሎሞንም እርሷንና ተከታዮቿን በጥሩ መስተንግዶ ተቀበላቸው፡፡ ንግሥት ሳባም የቤተ መንግሥቱን ሥርዓትና ሥጋዊና መንፈሳዊ ጥበቡን ቀሰመች፡፡ በኢየሩሳሌም ቆይታዋ ከንጉሡ ቀዳማዊ ምኒልክን ፀነሰች፡፡ ወደ ኢትዮጵያም ተመልሳ ልጇን ምኒልክን በዛሬዋ አሥመራ ከተማ አጠገብ እንደወለደችው ይነገራል፡፡

## የቀዳማዊ ምኒልክ ጉዞና የታቦተ ጽዮን መምጣት

ቀዳማዊ ምኒልክ ከአደገ በኋላ በ12 ዓመቱ ከእናቱ የተሰጠውን ለታቦተ ጽዮንና ለንጉሥ ሰሎሞን እጅ መንሻ ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዘ። ንግሥት ሳባም ለንጉሥ ሰሎሞን «ንጉሥ ሆይ ልጄን ሙሴ የጻፋቸውን ሕግጋት ሥርዓተ ክህነት አስተምረህ ላክልኝ።» የሚል መልእክት ልካ ነበር። ቀዳማዊ ምኒልክ በኢየሩሳሌም ከአባቱ ዘንድ ለሦስት ዓመት ያህል ቆይቷል። በዚሁ ዘመን መጻሕፍተ ሙሴን፣ ሕገ መንግሥትን፣ ሥርዓተ ክህነትን የዕብራይስጥን ቋንቋ ከሊቀ ካህናቱ ከሳዶቅ ተምሯል። ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስም በፈቃደ እግዚአብሔር ታቦተ ጽዮንን ይዞልን መጥቷል። ይህች ታቦት ለ3000 ዓመታት ያህል እስከዛሬ ድረስ በኢትዮጵያ በአክሱም ትገኛለች። ንግሥት ሳባም ታቦተ ጽዮን መምጣቷን ስትሰማ ለእግዚአብሔር መስዋዕት አቀረበች። ሰዎችን መርጣ ታቦተ ጽዮንን እንዲጠብቁ አድርጋለች። የመንግሥቱን ሥልጣን በሙሉ ለቀዳማዊ ምኒልክ አስረክባ ከዚህ ዓለም በሞት በተለየች ጊዜ በዚያዉ በአክሱም ተቀብራለች። ቦታውም እስከ አሁን ድረስ የንግሥት ሳባ መቃብር እየተባለ ይጠራል።

በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረው ታሪክ ጸሐፊው አቡሳላህ «አቢሲኒያውያን በእግዚአብሔር ጣቶች አሥርቱ ቃላት የተጻፈባት፣ ሁለት የድንጋይ ጽላቶች ያሉባት የቃል ኪዳኑ ታቦት አለቻቸው።» በማለት ጽፎ ነበር። በዘመናችን ይህችን ታቦት ፍለጋ ያደረገው ግርሃም ሐንኮክም «The sign and the seal» በተሰኘው መጽሐፉ ይህን ገልጦታል።

## ታቦተ ጽዮን በአክሱም

በኢትዮጵያ ታሪክ ልዩ ሥፍራ ከያዙት ቦታዎች ግንባር ቀደምትዋ የአክሱም ከተማ ናት። አክሱም የኢትዮጵያ የታሪክና የሃይማኖት እናት ከተማ ስትሆን ክክርስቶስ ልደት በፊት በ2ሺ ዓ.ዓ እንደተቆረቆረች መዛግብት ያስረዳሉ። አክሱም የቤተ ክህነቱም ሆነ የቤተ መንግሥቱ ማዕከል በመሆን ለብዙ ዘመናት አገልግላለች። በተለይም እግዚአብሔር ለሊቀ ነቢያት ሙሴ የሰጠው የታቦተ ጽዮን መንበር በመሆኗ ከተማዋን ድንቅ ሁኔታን ያጐናጽፋታል።

በዘመነ ሐዲስም የክርስትና መዲና፣ የስብከተ ወንጌል ማዕከል የጳጳሳት መንበር ለመሆን መቻልዋም በቤተ ክርስቲያናችን የታሪክ ክፍል ውስጥ እንደ አጥቢያ ኮከብ እንድታበራ አድርጎአታል። የአክሱም ከተማ የ4000 ዓመት ዕድሜ ያላት ሲሆን ስለ ስያሜዋም ሊቃውንቱ ሲያትቱ፡-

1. ከጌታችን ልደት በፊት 2000 ዓመት ገደማ የነበረውና የኩሽ የልጅ ልጅ /የኖኅ የልጅ፣ ልጅ ልጅ/ የሆነው አክሱማዊ ስሙን ለቆረቆሩት ከተማ ማውረሱ ይነገራል። ከተማውን በቆርቋሪው መሰየም የጥንት ሰዎች ባህል ነበር። ዘፍ.10፡1ጠ32
2. «አክሱም» የሚለው ቃል ከሁለት ጥንታውያን ቋንቋዎች የተገኘ ነው። «አኩ» በአገውኛ ቋንቋ ውኃ ማለት ሲሆን «ሱም» ደግሞ ከሴም ቋንቋ ተወስዶአል። ትርጉሙም «ሹም» ማለት ነው።
3. በሰሜን አክሱም አንድ የውኃ ጉድጓድ አለ። እሱም «ማይሹም» ይባላል። የከተማዋ መጠሪያ ከዚህ የተወሰደ ሳይሆን እንዳልቀረ አንዳንድ ሰቆች ይናገራሉ።
4. አክሱም /አ፡ ኩሽም- በዕብራይስጥ/ - ጥንታዊት፣ ቀዳማዊት የነገደ ኩሽ መዲና፣ አህጉረ ኩሽ ማለት ነው።
5. ገድለ መርቆሬዎስ ደግሞ «መካነ ዕንቁ ማለት ነው» ይላል።ለዚህም «ወበእንተዝ ተሰምየ ስማ ለይእቲ አክሱም፤ እስመ ትርጓሜሃ ለአክሱም መካነ ስም ብሂል ዝውእቱ መካነ ዕንቁ።»እንዲል።

የአክሱም ከተማ ታሪክ ይበልጥ እየገነነ የመጣው ከጌታችን ልደት በፊት 1000 ዓመት ገደማ ጀምሮ ነው። ምክንያቱም ይህ ዘመን ንግሥት ሳባ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ወደ ኢየሩሳሌም የተጓዘችበትና ልጇ ቀዳማዊ ምኒልክ ታቦተ ጽዮንን በጥበበ እግዚአብሔር ወደ ኢትዮጵያ ያመጣበት ዘመን በመሆኑ ነው።

## የጽዮን በዓል አከባበር

ኅዳር 21 ቀን በየዓመቱ በአክሱም ምእመናን በተገኙበት ታቦተ ጽዮን ዳጎንን ቀጥቅጣና ገለባብጣ ድል ያደረገችበት፣ ለእስራኤላውያን ተድላ ደስታን ያሰማችበት ለፍልስጥኤማውያን ደግሞ ኃይለ ተአምራቷን ያሳየችበት ነው። ከዚህም ሌላ ታቦተ ጽዮንን የኢትዮጵያን ምድር የረገጠችበት በመሆኑ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በስፋትና በጥልቀት ትምህርት ይሰጣሉ።

በዚሁ ዕለት የሚወሳው ሌላው ታሪክ ቀዳማዊ ምኒልክ ታቦቱን ይዞ አክሱም የገባበት፣ ንግሥት ሳባ ታላቅ በዓል አድርጋ የተቀበለችበት፣ አብርሃ ወአጽብሐ በአክሱም ከተማ 12 ቤተ መቅደስ ያለው ቤተ ክርስቲያን በአስደናቂ ሁኔታ ሠርተው ከጨረሱ በኋላ ቅዳሴ ቤቱን ያከበሩበት፣ እንዲሁም በ9ኛው መ/ክ/ዘመን ዮዲት ክርስትና ለማጥፋት በተነሳች ጊዜ በእርሷ ምክንያት ታቦተ ጽዮን ወደ ዝዋይ ሐይቅ የተሰደደችበት፡፡ በኋላም የሰላሙ ዘመን ሲመጣ ተመልሳ አክሱም የገባችበት በዚሁ በኅዳር 21 ስለሆነ በእነዚህ በተደራራቢ ታሪኮች ምክንያት በየዓመቱ በደመቀ ሁኔታ ይከበራል «ኅዳር ጽዮን በአክሱም ጽዮን» የሚባለውም ለዚህ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ ኅዳር 21 ቀን በታላቅ ክብር ታከብረዋለች፡፡ በዚሁ ዕለት የእመቤታችን ወዳጆች ምእመናን በዓሉን ለማክበርና ለመሳለም ወደ አክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን በብዛት ይገሠግሳሉ፡፡ ዕጣን፣ ጧፍ፣ ዘቢብ መባውን ይሰጣሉ፡፡ ካህናቱም ከዋዜማው ጀምረው በከበሮና በጸናጽል ስብሐተ እግዚአብሔር ያደርሳሉ፡፡ በድርሳነ ጽዮን መጽሐፍ ካህናቱ እንደተገለጠው በጽዮን ፊት እንደየመዓርጋቸው ቆመው «እግትዋ ለጽዮን ወህቅፍዋ» የሚለውን መዝሙር ከዳዊት እያውጣጡ ይጸልያሉ፡፡ይዘምራሉ፡፡ ፈጣሪያቸውን እያመሰገኑ የታቦተ ጽዮንን ተራዳኢነት በምእመናን ፊት ይመሰክራሉ፡፡

ታቦተ ጽዮን በእግዚአብሔር ፈቃድ በቀዳማዊ ምኒልክ ወደ ኢትዮጵያ ገብታ በአክሱም ከተቀመጠችበት ጊዜ ጀምሮ ሀገራችን በረከት፣ ረድኤት ሳይለያት በየዘመኑ የተነሱ ጠላቶችን ድል እያደረገች መልሳለች፡፡ እግዚአብሔር በታቦተ ጽዮን ላይ በረድኤት እያደረ የሕዝቡን ችግር እንዳስወገደ ሁሉ ዛሬም ችግራችንን እንዲያቃልልን፣ በረድኤት እንዲጐበኘን ዘወትር በጸሎት ታቦተ ጽዮንን ልንማጸን ይገባል፡፡ለእስራኤላውያን በታቦቱ ላይ እያደረ እየተገለጠ ያናገረ የባረከ የቅዱሳን አምላክ እግዚአብሔር አይለየን፡፡ አሜን፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

**ማኅበረ ቅዱሳን**